# “የኦሮሞ ህዝብ አኗኗር፣ የገዳ ድርጅት”

*(ከክቡር ኣቶ ይልማ ደሬሳ የታሪክ መጽሃፍ የተወሰደ)*

በኦሮሞ ህዝብ ልማድ ወንድ ልጅ ሁሉ በአመት የእድሜ ክፍያ ውስጥ ይደለደላል። ከ8 አመት ጀ ምረው እስከ 16 ኣመት እድሜ ውስጥ የሚገኙት ወንዶች ደባሌ በሚባል ክፍል ይመደባሉ። ከ16 እስከ 24 ኣመት እድሜ ውስጥ የሚገኙት ፎሌ በሚባለው ክፍል ይመደባሉ።

በ24ና በ32 ኣመት መካከል የሚገኙት ቆንዳላ በሚባል ክፍል ውስጥ ይመደባሉ። ከ32 እስከ 40 ዘመንውስጥ የሚገኙት ዶሪ በሚባለው ክፍል፣ ከ 40 እስከ 48 የሚገኙት ቡታ ካረዱ በኋላ ሉባ በ ሚባለው በመጨረሻው ክፍል ይመደባሉ። ይሄ በእድሜ ደረጃወንድ ልጅ የሚከፋፈልበትመደብ እ ያንዳንዱ 8 ኣመት ገዳ ይባላል። በጠቅላላው የድርጅቱም ስም ገዳ ነው።

እያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚገኙ 40 ኣመት ሲሞላቸው ቡታ ካረዱ በኋላ ሉባ ተብሎ የጎሳው የኣስ ተዳደር፣የፍርድና የጦር መምራትን ሃላፊነት ቀደምት ከነበሩ ሉባዎች ይረከባሉ። ቡታ የገዳን መለወጥ ለማክበር የኦሮሞ ህዝብ በየ 8 አመት ኮርማ ፣ድልብ፣ሰንጋና መሲናዎችን በኣያሌው አርዶ በትልቅ ድግስ የሚከበር በኣል ነው።

ህዝቡ የሚተዳደርበትን ኣዲስ ህግ የሚያወጡ፣ የነበረውንም ህግ የሚያሻሽሉ እነዚህ ሉባ የተባሉት ክፍል ናቸው። ዶሪ የተባሉት የሉባዎች ተከታይ የሆኑት ኣራት ኣመት ዶሪ ሆነው ከቆዩ በኋላ ጉቡ በሚባል ክፍል ገብተው ቡታ ከማረዳቸው ኣስቀድመው ባሉት በኣራት ዘመናት ውስጥ የጎሳውን ኣስተዳደር ፣ በደንብ ለማጥናትና ለመለማመድ ከሉባዎች ጋራ ይሰራሉ። ከደባሌ ኣንስቶ እያንዳንዱ ክፍል ወደ ከፍተኛው ደረጃ ለማለፍ የሚያጠናቸው የማህበራዊ ኣኗኗርና  የሚፈጽማቸው ስነ ስርዓቶች የተመደቡ ናቸው።

እላይ እንደተመለከተው ሁሉ የያንዳንዱ ገዳ እድሜ ስምንት ኣመት ነው። በጠቅላላው የገዳዎቹ ቁጥር ኣምስት ስለሆነ የመጀመሪያው ገዳ ዞሮ የሚደርሰው በኣርባ ኣመት ነው። ኣምስቱ ገዳዎች የየራሳቸው ስም ኣላቸው፣ ስማቸው ግን ኦሮሞዎች እየተባዙ ሄደው ከወላቡና ከኦዳ ነቤ እየራቁ ሲሄዱ  ተለዋውጧል። ሆኖም ስም ይለወጥ እንጂ ገዳ በስምንት ፣ ስምንት ኣመት መለወጡና የገዳዎች ቁጥር ኣምስት መሆኑና በጠቅላላውም የገዳዎች ዙሪያ በኣርባ ኣመት የሚፈጸም መሆኑ የማይንቀሳቀስ ደንብ ሆኖ እስከ ዘመናችን የቆየ መሰረታዊ ህግ ነው።

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ ገዳ ሲለወጥ የኦሮሞን ህዝብ የሚያስተዳድር  ኣባ ቦኩ የተባለው ዋናውን ስልጣን የያዘው ሹም ይለወጣል። ደግሞም መማክርቶችና ዳኞች የሚለዋወጡት በገዳ መለወጫ ጊዜ ነው። ገዳቸው ያለፈ ኣባ ቦኩ ፣ መማክርቶችና ዳኞች ከኣዲሱ ባለገዳዎች መካከል ለሚመረጡ ሹማምንት የህዝብን ማስተዳደር ስልጣን ያስረክባሉ። ካስረከቡም በኋላ ዩባ ወይም ኣካካዩ ተብለው ከኣዲሱ ባለገዳዎች ጀርባ ተቀምጠው በሽምግልና ይፈርዳሉ።

የስልጣን ኣረካከብ ስርዓት በሚከተለው ኣኳሃን ይፈጸማል። ገዳ የሚለወጥበት የቡታ በኣል ከመድረሱ ሁለት ኣመት ኣስቀድሞ ህዝቡ ኦዳ ከሚባል ከተከበረው ዛፍ ዙሪያ ይሰበሰባል። በስብሰባው ላይ ስልጣን የያዘው ኣባ ቦኩና መማክርቶች ፣ ዳኞችና ከሁለት ኣመት በኋላ ቡታ ለማረድ ተረኛ የሆኑት ባለገዳዎች በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ይደረጋል። በስብሰባውም ቦታ የቦረና ዘር የሆነ ኣባትና እናቱ ያልሞቱ፣ ሚስቱ በህይወት የምትገኝ፣ የበኩር ልጁም ያልሞተበት ፣ ኣካላቱ ያልጎደለ፣ የኣባቱና የልጆቹ ስም መልካም ስም የሆነ ደግ ሰው ከህዝቡ መካከል ተመርጦ ኣባ ኮርማ ተብሎ ይሾማል።

ህዝቡ በበኩሉ ከባለገዳዎች መካከል ሁነኛውን ሰው መርጦ  አባ ቦኩ ብሎ ይሾማል።ቀጥሎም መማክርትና ራባ ዶሪ የሚባሉ ዳኞች፣ አባ ዱላ የሚባል የጦር ሰራዊት መሪ ይመርጣሉ። ከምርጫው በኋላ አባ ኮርማው ለተሰበሰበው ህዝብ ንግግር \ለለቦ\ ካደረገ በኋላ ህዝቡን መርቆ ስርዓቱን ይፈጽማል። ከምረቃው በኋላ ህዝቦቹ እየዘፈኑ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ያሰናብታቸዋል። የዚህ የስብሰባ በአል የደጋጋ በአል ይባላል። ስምንት ኣመት ሲያስተዳድሩ ከቆዩት ስልጣን የሚረከቡ ሹማምንት  በህዝብ ከታወቁ በኋላ የሕግና የህዝብ ኣስተዳደር ጥበብ በጥልቀት ሲያጠኑ ይቆያሉ። በዚሁ ምክንያት ገዳ በተለወጠ ጊዜ የስልጣን መረካከብ ቀላል ስራ ይሆናል። ሹማምንቱም ስራቸውን በድንብ አውቀውት ይገኛሉ።

## ሕግ ስለ ማወጅ

በኦሮሞዎች ማህበር ውስጥ ህግ የሚያውጅ ድርጅት የሉባዎች ጉባኤ ነው። ጉባኤው ህግ ለማውጣት ተሰብስቦ የሚመክረው፣ በአንድ አንድ ጎሳ ውስጥ ከኣባ ቦኩ ደጅ ነው። በሌሎች ጎሳዎች ውስጥ ጉባኤው የሚደረገው ኦዳ ከሚባል ከታላቅ ዛፍ ጥላ ስር ነው። የሉባዎች ሰብሳቢ አባ ቦኩ ሆኖ ዶሪና ራባ የተባሉትም ኣለቆች ኣብረውት ይቀመጣሉ። አባ ቦኩ ቡሉኮውን ኣጣፍቶ ቦኩውን ከቡሉኮው ስር ደብቆ በርጩማ ከሚባል ወንበር ላይ ይቀመጣል። ሌሎቹ በጉባኤው ውስጥ ተካፋይ የሆኑት ሉባዎች ሁሉ በኣባ ቦኩ ዙሪያ ይቀመጣሉ።

የሚደነገገው የህግ ሃሳብ ለጉባኤው ከተነገረው በኋላ ስለቀረበው ህግ ሃሳባቸውን ለመስጠት የሚሹ ሉባዎች ሁሉ በየተራቸው ተነስተው  በመደገፍ ወይም በመቃወም ይሳተፋሉ። በጉባኤው ላይ ተራ የተሰጠው ተናጋሪ ከሸንጎው ፊት ሲቆም ጦሩን በግራ እጁ ጨብጦ በቀኝ የያዘውን ኣለንጋ ዋና ዋና ነገር በተናገረ ጊዜ እያስጮሄ ዲስኩር ያደርጋል። ተናጋሪው ዲስኩሩን ከጨረሰ በኋላ በንግግሩ ውስጥ ስሕተት አድርጎ እንደሆን እንዲያርምና የረሳውም ነገር ካለ እንዲጨምርበት ሲባል ሌላ ሰው ንግግር  ሳይጀምር ጉባኤው በጸጥታ ለተወሰነ ጊዜ ይጠብቃል። ንግግር ያደረገው ኣባል የማይቀጥል መሆኑ ሲታወቅ ለሚቀጥለው አባል ተራ ይሰጣል ። ከዚህ ስርዓት ወጥቶ ማንም ኣይናገርም።

የቀረበውን ህግ ለመቃወም ማንኛውም ሉባ መብት ኣለው። ነገር ይደር ለማለት የፈለገ ማንኛውም አባል  ቀቤ \ያዝኩ\ ያለ እንደሆን ይደር ብሎ ጉባኤው ይነሳል እንጂ ንግግሩ ኣይቀጥልም፣ ውሳኔም ኣይወሰድም። ህጉ ስርዓትን ተከትሎ ከተመረመረና የሚናገሩት ሉባዎች ሁሉ ከተስማሙበት በኋላ ጉባኤው ይዘጋል። በማግስቱ  አባ ቦኩ ኮርማ አርዶ  ቦኩውን የኮርማውን ደም ካስነካ በኋላ ''ሴራን ቱሜ'' ህግ ደንግጌያለሁ ሲል በጦሩ መሬቱን ከመታ በኋላ ህጉ እንደ ታወጀ ይቆጠራል።

## ፍርድ የሚፈጸምበት ስነ ስርዓት

በኦሮሞዎች ደንብ ስርዓትን የሚያዩና ባላገሮችን የሚያሟግቱ አባ ቦኩ ፣ ዶሪና ራባ የተባሉት የ ሉባዎች ዳኞች ናቸው። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ከሶስቱ ዳኞች ሌላ ከሳሹ ከሌሎች መካከል ሸኔየተባ ሉ ኣምስት ህግ አዋቂዎች ሲቀጥር ተከሳሹ ኣራት ቀጥሮ በጠቅላላው ሶስት ዳኞች፣ ዘጠኝ ሸኔዎች ሆነ ነው የሚያሟግቱት። ከእነዚህ ሌላ የፈቀደ ሰው ሁሉ በኣደባባዩ ላይ ተገኝቶ የፍርድ ሂደቱን ለመከታተል መብት ኣለው። ከተሟጋቾቹ ኣንዱ ሌላው የቀጠረውን ሸኔ ኣልቀበልም ለማለት ሶስ ት ጊዜ ደጋግሞ ሸኔው ኣይገባም ማለት ኣለበት። በሶስተኛው ጊዜ ኣይገባምብሎ ከተናገረ በኋላ ይህ ተቃውሞ የቀረበበት ተቆጣሪ ጠላቱ መሆኑን ወይም የባላጋራው ዘመድ መሆኑን ካላስረዳ በቀር ተ ቃዋሚው ለተቆጣሪው ሸኔ ዘጠኝ ላም ካሳ እንዲከፍልይፈረድበታል። ሸኔዎች ከተቆጠሩ በኋላ ከሳሽ ና ተከሳሽ አባ ኣለንጋ የተባሉ ጠበቃዎች ያቆማሉ። ህግ አዋቂ ሉባዎች ካልሆኑ በቀር ነገረተኞች እራሳቸው እንዳይሚገቱ ክልክል ነው።

ሙግት፣ ክርክር
በዚህ ኣኳሃን ከተከናወነ በኋላ “ተሬ” ከሚባል አደባባይ  ተሰብስበው ችሎት ያደርጋሉ ። ህግ በ
ሚያወጡ ጊዜ እንደሚደረገው ሁሉ ሙግት ሲደረግ ማንኛውም ሰው ተነስቶ ቀቤወይም ያዝኩ ያለ
እንደሆን ሙግቱ ማደር ኣለበት።

ተሟግቶ የተፈረደበት ሰው ይግባኝ ያለ እንደሆን ይግባኙ በጎሳው ፍርድ ቤት ሊታይ አይችልም።
የሚበዛውን ጊዜ ይግባኝ ፍርድከኣንዱ ጎሳ ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ጎሳ ፍርድ ቤትይላካል። ኦሮሞ
ዎች ሁሉ በኣንድ ሰፈር ወላቡ ዙሪያ በነበሩ ጊዜ ነገርን ከኣንዱ ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ጎሳ ዳኘነ
ት መውሰድ ቀላል ነበር። በኋላ ግን ነገዱ ተከፋፍሎ ጎሳዎቹ ከተራራቁ በኋላለምሳሌ ከመጫ ነገድ
 ፍርድ ቤት ወደ ቱለማ ለመላክ ኣስቸጋሪ ሁኔታ ፈጠረ። ይህን ችግር ለማስወገድ የሚከተለው ደ
ንብ ተደነገገ።

ስርዓታቸውን ወደ ሌላ ጎሳ ፍርድ ቤት ለይግባኝ የሚወስዱ ነገረተኞች ሁሉ በዘንጋቸው ላይ ጨር
ቅ እንደባንዲራ እያሰሩ እንዲጓዙ ፣ በጉዟቸውም ጊዜ ይህን ምልክት ያየ የኦሮሞ ቤተስብሁሉ ተቀ
ብሏቸው ኣብልቶ፣ አጠጥቶ ፣ አሳድሮ እንዲሸኛቸውና መንገድም እንዳይሳሳቱ እንዲመራቸው ተደ
ረገ። በሚያልፉበት ሃገር ቀማኛ ወይም ወንበዴ ከጎዳና ላይ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ የሃገሩ ሞቲ ሰ
ዎች ኣስከትሎ ከኣደገኛው ቦታ እንዲያሳልፋቸው በሴራ ቱማ ተደነገገ። ይግባኝ ባይ በሚጓዝበት
መንገድ ባንዲራውን ይዞ ከተጓዘ ችግር እንዳያገኘውና ፍርዱምበስርዓት እንዲታይለት ጥብቅ ህግ
ሆኖ የቆየ ነው ‘’ ።

ከዚህ በላይ የተመለከተውን የወስድኩት ‘’የኢትዮድያ ታሪክ በኣስራ ስድሰትኛው ክፍለ ዘመን’’
ከሚለው በኣቶ ይልማ ደሬሳ ከተዘጋጀው የታሪክ መጽሃፍ ነው። ይህ መጽሃፍ የታተመውበኢትዮ
ድያ ቆጣጠር በ1959 ነው። በንጉሱ ዘመን ኣቶ ይልማ ደሬሳ ክቡር ኣቶ ይልማ ደሬሳ ይባሉ የነበ
ሩ፣ከእንግሊዝ ሃገር ዩኒቨርሲቲ በምጣኔ ሃብት (economics) ሙያ
የተመረቁና የመጀመሪያው ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ የኢትዮድያ የገንዘብ ሚንስትር የነበሩ ሰ
ው ናቸው ይባላል።

ክቡር ኣቶ ይልማ ደሬሳ ከጻፉት ታሪክ ውስጥ ከላይ የሰፈረውን ወስጄ ለኣንባቢያን ለማካፈል ያነ
ሳሳኝ በቅርቡ ‘’የወደፊቷ ኢትዮድያ’’ በሚለው ኣንድ ስብሰባ ላይ ፕሮፌሰር እዝቄል ገቢሳኢት
ዮድያ ከተመሰረተችበት ዘመን ኣንስቶ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ያልታየባትና ሁልጊዜም በግጭ
ት ወይም በጦርነት መሆኑን በመግለጽ ለዚህም ዋናው ምክንያት ሃገር በቀል የሆኑ የህዝቦችን የመ
ቻቻልና የኣስተዳደር ባህሎችን በመጠቀም ችግሮችን የመፍታት ኣሰራሮችን ባለማዳበራችንና የዉ
ጭ እየቀዳን   በመቆየታችን ነው በሚል \ቃል በቃል ባይሆንም\  ያቀረቡትኣስተያየት ነው።
ፕሮፌሰር እዝቄል የጥንት ሃገር በቀል ከሆኑት የህዝብ ኣስተዳደር ስርዓቶች ውስጥ የኦሮሞ የገዳ
ስርዓትን ጠቅሰዋል። እኔም ይህንኑን መነሻ በማድረግ ስለዚህ ስርዓት ያለንን ግንዛቤ ለማደስ
ይረዳል ብዬ ስለገመትኩ ክቡር ኣቶ ይልማ ደሬሳ የገዳ ስርዓትን ኣስመልክተው
ያሰፈሩትን  ለአንባቢያን ለማካፈል ፈለኩ።እንደዚሁም እስካሁን የገዳ ስርዓትን ኣስመልክቶ
እንደዚህ በቅደም ተከተል በኣጭሩ ግልጽ ተደርጎ ለኣማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለመቅረቡ
እርግጠኛ ስላልሆንኩ ለእነሱ መረጃ ለመስጠት ይረዳል በሚል ነው።

በተለይም ኣዲሱ ትውልድ ስለዚህ እጅግ ሰብዓዊና ፍትሐዊ ስለሆነው የገዳ ስርዓት አስተዳደር
የሚያውበቅት መንገድ ያለ ስለማይመስለኝም ጭምር ነው። ሌላው እኛ የዚህ ኣኩሪ ታሪክ ባለቤት
የሆን ኦሮሞዎችም በኣፍ ብቻ ሳይሆን በተግባር ስራ ላይ በማዋል ቀዳሚ ሆነን መገኘት ኣለብን
በማለት ለማሳሰብ ነው።

ሌላው ይህ ከብዙ መቶ ኣመታት በፊት ቀርቶ በዛሬው በ21ኛው ክፍለ ዘመን
እንኳን በስራ ላይ ያልዋለ የኣስተዳደርና የፍትሕ ስርዓት ኣደረጃጀት ምን ያህል የተራቀቀ መሆኑ
ን የዛሬውትውልድ እንዲያጤነው በመፈልግ ነው። በተጨማሪም ፕሮፌሰር እዝቄል በስብሰባው ላይ

**እንደተናገሩት “ሃገር በቀል በሆኑ እሴቶቻችን ከኣሁኑ ሁኔታ ጋር ኣጣጥመን መጠቀም እንችላለን ያሉትንም የዛሬው የኢትዮድያ ፖለቲከኞች በሚገባ ቢመረምሩት ለኢትዮድያ የዘመናት የፖለቲካ ጭቅጭቆችና ሰላም ማጣት መፍትሄ ሊገኝ ይችል ይሆናል የሚልም ተስፋ ስላደረኩ ነው።**

**ስለዚህ ፕሮፌሰር እዝቄል ገቢሳ ለተሰብሳቢዎቹ ሲናገሩ “ይህ የገዳ ስርዓት የኦሮሞ ብቻ ኣይደለም የናንተም ነውና ልትኮሩበት ይገባል” ባሉት መሰረት**
**ይህ እጅግ ረቂቂና ፍጹምፍትሐዊ የሆነ የህዝብ ኣስተዳደርና የፍትሕ ስርዓት ታሪካችንን ወደኋላ ተመልሰን አሁን ኢትዮድያን ከገጠማት ኣጠቃላይ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ምስቅልቅሎች ለመውጣት ይረዳናል በሚለው ላይ መምከር ያስፈልጋል።**

**በመጨረሻምእግረመንገዴን ዶክተር ሃይሌ ላሬቦ የተባሉት’’ ምንሊክን ቢትወቅሱ ማንነታችሁን ትረሱ’’ ብለው በ**2014 **በኢትዮሚዲያ ላይ ባሳተሙት ጽሁፍ “የገዳ ስርዓት የተባለው ኣሳፋሪ ነው”፣ “ገዳ ማለት ግዲያ ነው” ብለው በጥላቻ እንደጻፉት**
**ሳይሆን የኦሮሞ የገዳ ስርዓት በእጅጉ የሚያኮራ፣ በዛሬው ዘመን እንኳን በየትኛውም ክፍለ ኣለ ም ስራ ላይ ያልዋለ ህዝባዊ የአስተዳደርና የፍትሕ ስርዓት መሆኑን እንዲያውቁት ለማሳሰብ ነው። ክቡር ኣቶ ይልማ ደሬሳ ከዛሬዉ የፖለቲካ ወገናዊነት ኣንጻር ሳይሆን ያዩትንና ያለፉበትን እዉነተኛ የህዝብ ታሪክ የጻፉ መሆናቸውንም ዶክተር ሃይሌ ላሬቦ ይረዳሉ ብዬ እገምታለሁ።**

**በቀለ ጅራታ**

**የቀድሞው የኦፌዴን ዋና ጸሃፊ**
**Bekelejirata2010@gmail.com**